# ውለታሽ ሲያቃጭል !!!

ከተዘራ አሰጉ/ ከምድረ እንግሊዝ/

ትዝታ በለሆሳስ ሲታጀል
ህልም በይሆናል ሲማስን ።

ርቆ ኮቴ
ሲኖሩ በህሳቤ ።

አዕምሮ ሲያንሰላስል
በምኞት ሲባክን።

ጅሮን ሰጥቶ
ተባለን ሰንቆ ።

ለመጓዝ ሲያኮበኩቡ
ዕውነታን ሊያስረግጡ ።

ቆርጠው ሲነሱ
የሩቁን ጎዳና ሊያቋርጡ ።

ከራስ ጋር ሙግቱ
በወሬ ቋት መታመሱ ።

ቆርጠ ቀጥል ውለ ቢሱ
ያልሆነውን ማዳወሩ ።

ያላዩትን እንዳዩ
የሆነውን አሌ እያሉ ።

ውዥንብር መፍጠሩ
ክፉ ሰቆቃን ማረዩ ።

ልብ ሸቶ መታደም
በምን ይሉኝ መወዛገብ ።

ባሉባልታ መሸማቀቅ
እያጡ ራስን መሆን ።

ለማየ ለሩርህዋ
ሳይኖራት አንኩ ብላ ፤

አባየ መሬት ገፍቶ
ግሮ አስተምሮ ፤

ሲያቃጭል አደራ ፤ ወለታው
የአደራ ክፋይ ቁርሾው ፤

አይደረስ የለም ተደረስ
የሩብላው አታሞ አደበ ፤

ሲተካ በእዕዋፍ ቅላፄ
በፈረሱ ጉግስ ዝማሬ ፤

የኮርማው የጥጃው ዋካታ
የወተት የዕርጎው ምግታ ፤

ሞፈር ቀንበሩን ማዋደሩ
ማረስ በደቦ መጎልጎሉ ፤

የናፍቆት ጓዝ ሲራገፍ
ነፍስ በሃሴት ሲጀቦን ፤

የቀድሞን ስንክሳር ሲያጠነጥኑ
የጉልምስናን ማህደር ሲያሰባጥሩ ፤

ኢትዮጵያየ ምሳሌ ገነት
መኩሪያ የኛነታችን ማገር ፤

አሁንማ ዛሬ ተሞሸረሽ
አሸራሽን መልሰሽ ፤

የላሊበላ የአክሱም
የፋሲለደስ የሐረር ግንብ ፤

የሶፍዑመር የብሔር ብሄረሰቦችሽ
ፈርጥ መገለጫ አንችነትሽ ፤

በዳግም ስልጣኔ ታጅበሽ
በኑልኝ በኑሩብኝ አስደምመሽ ፤

ሲደርሱ ከሳንቃው በርሽ
ሲያስፈንድቅ የልብን ምት ፤

ዕንባ ቀረር ሲል
ናፍቆት ሲያብከነክን ፤

ዐይን ቅድብ ሲወጠር
ዙሪያ ገቡን ሲያማትር ፤

ከተማው ተመንድጎ
አስፋልቱ ተለስኖ ፤

ሁከት አሉባልታ
ተፎርሾ በእውነታ ፤

አዘመራሺ አምሮ
እዳሴሽ ጎምርቶ፤

ማቃጨል ሲጀምር
አዕምሮ ሲጠይቅ ፤

እርሾ አስተዋፅኦን
ምን አርኩን ሲጭር ፤

ህሊናን ስያሟግት
ቁጭትን ስያዳውር ፤

ከዚህም ከዚያ ክሊኒኩ
ትምህርት ቤት ኮለጁ ፤

ከእምየ በር ድጅ
ከአደኩበት ከገጠሩ ፤

ባጃጁ ማድረሱ
በአፍታ በቅፅበቱ ፤

አባየ ሲለኝ አሎ
ሞባይሉን ወድሮ ፤

እንግዲህ ወገኔ
ለአንተ ና ለኔ ፤

ባሉባልታ ልፋፌ
ሳትታጀል በወሬ ፤

ግዜ አልፎ ሳይቀድምን
ፀፀት ከመሰነቅ ፤

የዕድገቷ ተቋዳሽ
አሽራህም እንዲያርፍ ፤

ለሃገርህ ስትል
ሳይኖር ለሰጠችህ ፤

ጥሪትህም ይፍሰስ
ዕውቀትህም ይድረስ ፤

ምንም ቢማስኑ
ጨረቃ ቢደርሱ ፤

ማን እንደ ኢትዮጵያ
አቅፋ አጉራሽቱ ።

ከተዘራ አሰጉ /ከሃገረ እንግሊዝ/